በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ ብድር አሰጣጥ፣ አጠቃቀም እና አሰባሰብን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ገፅ

መግቢያ 1

የኤጀንሲው ዓላማ 1
የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር 2
የኤጀንሲው አደረጃጀት 3
የሰው ኃይል 4
የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ 4

የኦዲቱ ዓላማ 4

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ 5

የመንግስት ትርፍ ድርሻ አሰባሰብና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አሰጣጥ፣ አጠቃቀምና አሰባሰብ የስራ ሂደት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION) 5

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ 6

የኦዲቱ ዋና ትኩረት አቅጣጫዎች 6

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት 7

የኦዲት ግኝቶች 9

ኤጀንሲው የመንግስት ትርፍ ድርሻ አሰባሰብ፣ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር አሰጣጥ፣ አሰባሰብ እና አጠቃቀምን በተመለከተ እስትራቴጂክ ዕቅዱን መሠረት በማድረግ አመታዊ እቅድ የሚያዘጋጅ መሆኑን በተመለከተ፤ 10
ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች እና አክስዮን ማህበራት የመንግስት ትርፍ ድርሻን ፈሰስ ማድረጋቸውን መከታተሉን በተመለከተ፣ 12
ኤጀንሲው ለመንግስት የልማት ድርጅቶች እና አክሲዮን ማህበራት በብድር የሰጠው ሂሳብ ውጤት ያስገኘ ስለመሆኑ መከታተሉን በተመለከተ፣ 14
ኤጀንሲው የፀደቁ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የሚሰጡ ብድሮችን ለድርጅቶቹ ገቢ ማድረጉንና በወቅቱ ማሳወቁን በተመለከተ፣ 15
ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች የፈንድ አጠቃቀም ከታለመለት ዓላማ ውጭ ውሎ ሲያገኝ የማስተካከያ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን በተመለከተ፣ 17
ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች የፈንዱ ሂሳብ በየአመቱ በውጭ ኦዲተር እንዲያስመረምሩ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ 19
ኤጀንሲው ለመንግስት ልማት ድርጅቶች ብድር በሚሰጥበት ጊዜ የብድር ውል ስምምነት የሚያስገባ መሆኑን በተመለከተ፣ 20
ኤጀንሲው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ በሚዞሩበት ጊዜ ያለባቸውን የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድና የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሂሳብ እንዲከፍሉ ውል የሚያስገባ መሆኑን በተመለከተ፣ 24
ለ. የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አዋጆችን ፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን ተፈጻሚ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የሚሰሩበት ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርአት የተዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ 28
የፈንድ አጠቃቀም ግምገማ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣ 28

የመደምደሚያ ሃሳቦች 30

የማሻሻያ ሃሳቦች 33

አባሪ I

የኦዲቱ የመመዘኛ መስፈርቶች

አባሪ 2

የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሂሳባቸውን ያዘገዩ የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ዝርዝር

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. መንግስት በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን የተለየ ሚናና ተሳትፎ ባገናዘበ መልኩ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ድርሻ በማስፋት የአገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት ለማፋጠን እንዲሁም የልማት ድርጅቶች በመንግስት ይዞታ ስር እስካሉ ድረስ ተወዳዳሪና አትራፊ ሆነው የአገሪቱን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በማስፈፀምና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በማምጣት ረገድ ተገቢ ሚና እንዲጫወቱ አመራርና ድጋፍ መስጠት ተገቢ በመሆኑ ቀደም ሲል በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በኢኮኖሚ ጉዳይ ዘርፍ ውስጥ ተደራጅቶ በተመደበለት የስራ አመራር ቦርድ እየተመራ የነበረው የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ጽ/ቤት የፌዴራል አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ማሻሻያ በተደረገበት በ1994 በጀት ዓመት ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ወጥቶ ራሱን ችሎ በአዋጅ ቁጥር 277/1994 የባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ሆኖ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡

2. ከዚህም በመቀጠል የፕራይቬታይዜሽንን አፈፃፀምና የመንግስት ልማት ድርጅቶችን የመቆጣጠር ተግባርን ማቀናጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ /ኢፕኤ/ እና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን /መልድተባ/ አንድ ላይ ተጣምረው በአዋጅ ቁጥር 412/96 መሰረት የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የአሁኑ ኤጀንሲ /ፕመ ልድተኤ/ አንድ ራሱን የቻለ የፌዴራል መስሪያ ቤት ሆኖ ተቋቋመ፡፡

የኤጀንሲው ዓላማ

3. ኤጀንሲው የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር 412/1996 መሰረት:-

- የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም ግልጽና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም ማድረግ፣

- የመንግስት የልማት ድርጅቶች አቅማቸውን በተሻለ ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ማስቻልና የተሻሻሉ የማኔጅመንት ሥርዓቶችንና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሥራ አፈፃፀማቸው እንዲሻሻልና የላቀ ውጤት እንዲያመጡ ማገዝ፣
- በተለያዩ ምክንያቶች የግል ባለሀብቶች ሊሳተፉባቸው ባልቻሉና ለኢኮኖሚው አጠቃላይ ልማት ማነቆ ሊሆኑ በሚችሉ ዘርፎች የልማት ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ማድረግ፣
- የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አመራር መቆጣጠር እና በመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክስዮን ማህበራት የመንግስትን የባለቤትነት መብት ማስከበር ናቸው፡፡

የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

4. አግባብነት ያላቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 እና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኤጀንሲው በአዋጅ ቁጥር 412/1996 የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

- በአዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀፅ 5 (3) መሰረት የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የፕሮጀክት ጥናቶችን ያካሂዳል፣
- ከመንግስት ጋር በቅንጅት ኢንቨስት ለማድረግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች የሚያቀርቧቸውን የፕሮጀክት ሃሳቦች ገምግሞ ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ያስፀድቃል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣
- የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አቅም ለመገንባት የሚረዱ ጥናቶችን በማካሄድ አጠቃላይ መመሪያዎችን ይሰጣል፣
- የመንግስት የልማት ድርጅት የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢና አባላትን ይመድባል፣ ያነሳል አበላቸውንም ይወስናል፡ ሆኖም የአዋጅ ቁጥር 25/1992 የአንቀፅ 12 (2) ድንጋጌ ላይ (ከቦርድ አባላት መካከል ቁጥራቸው ከአንድ ሶስተኛ የማይበልጥ የሚሆኑ አባላት የሚመረጡት በሰራተኞች ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል፡፡ ሌሎች አባላት በተቆጣጣሪው ባለስልጣን የሚመደቡ ይሆናል) አክስዮኖች ሙሉ በሙሉ

በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ የአክስዮን ማህበር የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምደባ በሚመለከትም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፣

- የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የውጭ ኦዲተሮች ምደባ ያፀድቃል፣
- የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አጠቃላይ ግቦችና የኢንቨስትመንት እቅዶች ያፀድቃል፣
- የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣
- በውጭ ኦዲተሮች የተመረመሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ ምርመራ ያፀድቃል፣
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ከመዝገብ ስለሚሰረዝበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
- የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ማዋሃድ ወይም መከፋፈል ሲያስፈልግ ተገቢውን ጥናት አካሂዶ ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣
- ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የስራ አመራር ቦርድና የማኔጅመንት አባላት ተፈፃሚ የሚሆን በውጤት ላይ የተመሰረተ የማበረታቻ ስርዐት ይዘረጋል፣ በስራ ላይ እንዲውልም ያደርጋል፣
- በአክስዮን ማህበራት የባለአክስዮኖች ጉባኤ መንግስትን ይወክላል፣ በመንግስት በኩል የሚቀርቡ የዲሬክተሮች ቦርድ እጩ አባላትን ይሰይማል የሚሉ ናቸው፡፡

የኤጀንሲው አደረጃጀት

5. ኤጀንሲው በአንድ ዋና ዳይሬክተር በሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክቶሬቶች የሚመራ ሲሆን ተጠሪነቱም ለፕራይቬታይዜሽን ቦርድ እና ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፡፡ በኦፕሬሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዘርፍ ስር 2 ዳይሬክቶሬት፣ በፕራይቬታይዜሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ስር 2 ዳይሬክቶሬቶች እና 9 ቡድኖች እንዳሉት ለመረዳት ተችሏል፡፡

የሰው ኃይል

6. ኤጀንሲው ባካሄደው መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት 332 የስራ መደቦች እንደሚኖሩት በመዋቅሩ ተቀምጧል፡፡ ከዚህም ውስጥ እስከ ታህሳስ 30/2005 ዓ.ም ድረስ 205 የስራ መደቦች በሰው ሃይል የተሟሉ ሲሆን ቀሪው 127 መደብ በክፍትነት ይታይል፡፡ በሰው ሃይል ከተሟላው የስራ መደብ ውስጥ 90 ወይም (44% በመቶ) ሴቶች ሲሆኑ 115 ወይም (56%) ወንዶች ናቸው፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ በኤም.ኤስ.ሲ/ኤም.ኤ ደረጃ ያሉ 20 (10%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 88 (43%)፣ ኮሌጅ ዲፕሎማ 42 (20%) እንዲሁም ከዲፕሎማ በታች 55 (27%) ናቸው፡፡

የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ

7. ኤጀንሲው ስራውን ለማከናወን ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን በ2001፣ በ2002 ፣ በ2003 እና በ2004 በጀት ዓመታት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የተፈቀደለት መደበኛ በጀት እንደቅደም ተከተሉ ብር 6,365,900፣ 6,125,400 ፣ 8,925,689 እና 14,953,700 በድምሩ 36,370,689 ሲሆን በ2001 ዓ.ም ብር 6,036,270 በ2002 ዓ.ም ብር 5,887,965 ፣ በ2003 ብር 8,466,321 እና በ2004 በጀት ዓመት ብር 11,770,526.93 ስራ ላይ አውሏል ፡፡

የኦዲቱ ዓላማ

8 የኦዲቱ ዓላማ የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ ብድር እና ድጋፍ አሰጣጥ፣ አሰባሰብ እና አጠቃቀም በህጉ መሰረት በአግባቡ መከናወኑን እና ይህንኑ ሥራ ለማከናወን ሃላፊነት ና ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ሃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን እና በቅንጅት መስራታቸውን እንዲሁም ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርአት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ሲሆን ፤ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

9 ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ዋና መ/ቤት ሲሆን ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ፣ ከሸቀጦች ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት፣ ከባህርዳር፣ ኮምቦልቻ፣ አዋሳ ጨርቃ-ጨርቅ ፣ ከአትክልትና ፍራፍሬ ገበያ ፣ ከባቱ ኮንስትራክሽን ፣ከኮስቲክ ሶዳ ፣ ከአዳሚቱሉ ፀረ -ተባይ ማዘጋጃ ፣ ከኢትዮጵያ ቆዳ ፣ ከታቦር ሴራሚክ ውጤቶች ማምረቻ አክሲዮን ማህበራት የስራ ሃላፊዎች ጋር የኦዲት ቡድኑ ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ማስረጃዎችን በመከለስ በድምሩ ከ13 ቢሮዎች መረጃዎች ተሰብስበዋል። ኦዲቱ የሸፈነው አራት የበጀት ዓመታት ከ2001 እስከ 2004 ዓ.ም ባለው ጊዜ የመንግስት ትርፍ ድርሻ አሰባሰብ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር አሰጣጥ ፤ አመላለስና አጠቃቀምን በተመለከተ የተከናወኑ ስራዎችን ነው።

የመንግስት ትርፍ ድርሻ አሰባሰብና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አሰጣጥ፣ አጠቃቀምና አሰባሰብ የስራ ሂደት መግለጫ (process description)

10 የኮርፖሬት አመራር የስራ ሂደት ዳይሬክቶሬት በስሩ የእቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም ክትትል፣የቦርድ አመራር የመመሪያ ዝግጅት ትግበራ እና ኮርፖሬት ፋይናንስና ፈንድ አስተዳደር ቡድኖች የሚገኙ ሲሆን የእቅድ ዝግጅት ፤የአፈፃጸም ክትትል ቡድን ስትራቴጂያዊና ዓመታዊ እቅድ በልማት ድርጅቶች እንዲዘጋጅ ያደርጋል ይከታተላል የሩብ ዓመትና ዓመታዊ የእቅድ አፈፃፀምን ይገመግማል የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል / እንዲወሰድ ያደርጋል።

11 የቦርድ አመራር የመመሪያ ዝግጅትና ትግበራ ቡድን የስራ አመራር ቦርድ አባላት ለልማት ድርጅቶች ብቁ አመራር እየሰጡ ስለመሆኑ ይከታተላል ልማት ድርጅቶችን ለመምራት የሚያስችሉ አስፈላጊ ደንቦችና መመሪያዎችን በጥናት ለይቶ እና አዘጋጅቶ ያፀድቃል::

12 የኮርፖሬት ፋይናንስና ፈንድ አስተዳደር ቡድን ዓመታዊ እቅድ ያዘጋጃል የልማት ድርጅቶችን የፋይናንስ ስትራክቸርና የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ጥናት ያካሂዳል ዲስክሎዠ የሚደረጉ መረጃዎችን ለይቶ ያጠናቅራል ለውሳኔ ያቀርባል ለህብረተሰብ እና ለመንግስት የሚሰራጩበትን የአሰራር ስርአት ይዘረጋል የፋይናንስ መረጃዎችን የአፈጻጸም ሪፖርት ያዘጋጃል የሚዋሀዱ ፣ የሚከፋፈሉና የሚፈርሱ የልማት ድርጅቶችን ጥናት ያካሂዳል በጥናቱ መሰረት የልማት ድርጅቶችን የፋይናንሽያል ስትራክቸር እንዲስተካከል የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል ፡፡ የውጪ ኦዲተሮችን የምደባ ፕሮፖዛል አዘጋጅቶ ለውሳኔ ያቀርባል በውጪ ኦዲት ሪፖርት ግኝት መሰረት በልማት ድርጅቶች የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን ይከታተላል ያረጋግጣል፡፡

13 ከልማት ድርጅቶች የሚቀርቡ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ጥያቄዎችን ገምግሞ ለውሳኔ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በማቅረብ ፈንዱ ለተፈቀደላቸው ድርጅቶች ገንዘብ እንዲከፈል ያደርጋል እንዲሁም የፈንድ አጠቃቀሙን ይከታተላል ይገመግማል የአፈጻጸም ሪፖርት አዘጋጅቶ በውጪ ኦዲተር ያስመረምራል፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ

14 ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ አሰባሰብ፣ ብድር አሰጣጥ እና አጠቃቀም ኢኮኖሚያዊ ፤ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

የኦዲቱ ዋና ትኩረት አቅጣጫዎች

15 ከላይ በተገለፀው የኦዲት አካባቢ ሥር ሁለት ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች የተለዩ ሲሆን በመጀመሪያው የትኩረት አቅጣጫ ሥር ሁለት ንዑስ ትኩረት አቅጣጫዎችና በሁለተኛው ትኩረት አቅጣጫ ስር አንድ ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡

1. የመንግስት የትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ አሰባሰብና አጠቃቀምን በተመለከተ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም

የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዐት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፡፡

1.1 ኤጀንሲው ከመንግስት ልማት ድርጅቶች እና አክሲዮን ማህበራት በየበጀት ዓመቱ የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና ለኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የሰጠውን የብድር ሂሳብን በወቅቱ ለመሰብሰብ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ እና ቀልጣፋ የአሰራር፣ የቁጥጥር እና የክትትል ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣

1.2 ኤጀንሲው የመንግስት የትርፍ ድርሻ አሰባሰብ ና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድን ለልማት ድርጅቶች እና አክሲዮን ማህበራት የሚሰጥበትን የብድር አሰጣጥ፣ አመዘጋገብ፣ አጠቃቀም እና አመላለስን ውጤታማ ማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱ እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣

2. የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አዋጆችን ፤ ደንቦች እና መመሪያዎችን ተፈጻሚ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የሚሰሩበት የአሰራር ስርዐት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርአት የተዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፡፡

2.1 ኤጀንሲው ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ከመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ አክሲዮን ማህበራት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ የመወያያ መድረክ፣ ዕቅድ እና የዕቅድ ክንውን ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉ ናቸው

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት

16 በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሁለት ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን እና ሶስት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 28 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የተለያዩ መመሪያዎች፣ እና በኤጀንሲው የተጠናው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት

ሰነድ እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው። በተዘጋጁት የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የፕራየቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ሃላፊዎች አስተያየት ሰጥተውበታል። መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዟል።

ክፍል#ሁለት#

የኦዲት ግኝቶች

ሀ. የመንግስት የትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ሂሳብ አሰባሰብና አጠቃቀምን በተመለከተ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዐት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

ኤጀንሲው የመንግሥት የትርፍ ድርሻ አሰባሰብ፣ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አሰባሰብ፣ ብድር አሰጣጥ እና አጠቃቀምን በተመለከተ የሚያከናውነውን ተግባር በእስትራቴጂክ ዕቅዱ ውስጥ ማካተቱን በተመለከተ

17. ኤጀንሲው የመንግስት ትርፍ ድርሻ አሰባሰብን እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ አሰባሰብ፣ ብድር አሰጣጥና አጠቃቀም በተመለከተ የሚያከናውነውን ተግባር በስትራቴጂክ እቅድ ውስጥ ሊያካትትና ተግባራዊ መደረጋቸውን በየአመቱ ሊያረጋግጥ ይገባል፣

18. ኤጀንሲው ከ2003-2007 ባዘጋጀው እስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ሂሳብ በየዘርፉ በዝርዝር ለምን ያህል አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ብድር እንደሚሰጥ እና ምን ያህል የብድር ተመላሽ እንደሚሰብሰብ የልማት ድርጅቶችንና አክሲዮን ማህበራትን የፍላጎት ጥናት መሰረት በማድረግ በስትራቴጂክ እቅዱ ውስጥ ያላካተተና በየአመቱ ተግባራዊ መደረጋቸውን የማያረጋግጥ መሆኑን ከተከለሱት ሰነዶች ለመረዳት ተችሏል።

19. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ስትራቴጂክ እቅድ ሲዘጋጅ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ደረጃ ላሉ ተቋማት ስትራቴጂክ እቅድ ምሰሶዎች (pillars) ጸድቀው ስለሚላኩና ኤጀንሲው በዚህ መሰረት እንዲሰራ ስለሚጠየቅ በስትራቴጂክ እቅድ አለመካተቱን፣ ነገር ግን በ2003-07 ሚዛናዊ ውጤት ተኮር (BSC) ውስጥ የሚሰሩ ስራዎች በዝርዝር በመካተታቸው በብድር ሊሰጥ የሚገባው የብድር መጠኑንም በተመለከተ በደንብ ቁጥር 107/1996 በየበጀት

ዓመቱ ከድርጅቶች ከሚገኘው ትርፍ 40% ለኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ እንደሚውል ገልፀዋል፡፡

20. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጸደቀው በሚሰጡት የስትራቴጂክ እቅድ ምሰሶዎች መሰረት በስትራቴጂክ ዘመኑ የሚሠራውን ስራ በስትራቴጂክ ዕቅዱ ውስጥ አካቶ መያዝ ሲገባው ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ስለ ሚሰጠው የብድር መጠን፣ ብድሩን ስለሚያገኙ አክስዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች እንዲሁም ከብድሩ ተመላሽ ስለሚደረገው የገንዘብ መጠን ራሱን በቻለ መልኩ በስትራቴጂክ ዕቅዱ ውስጥ ባለማካተቱ እና በየበጀት አመቱ ባለመረጋገጡ በብድር አሰጣጥ፣ አጠቃቀም እና አሰባሰብ ላይ በየጊዜው የሚያጋጥሙ ችግሮችን በወቅቱ ለማስተካከል የሚያስችል የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የእስትራቴጂክ እና የየበጀት ዓመቱን እቅድ አፈፃፀም ውጤታማነት ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

21. ይህንኑ በተመለከተ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የሚገኘውን ሂሳብ በዋነኝነት ለኮልፎስፌትና ጎማ ዛፍ ፕሮጀክት እንዲውል ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር መስማማታቸውን ታሳቢ በማድረግ በእቅዱ ውስጥ አለማካተታቸውን ገልፀዋል፡፡

ኤጀንሲው የመንግስት ትርፍ ድርሻ አሰባሰብ፣ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር አሰጣጥ፣ አሰባሰብ እና አጠቃቀምን በተመለከተ እስትራቴጂክ ዕቅዱን መሠረት በማድረግ አመታዊ እቅድ የሚያዘጋጅ መሆኑን በተመለከተ፤

22. ኤጀንሲው የመንግስት ትርፍ ድርሻ አሰባሰብ፣ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር አሰጣጥ፣ አሰባሰብ እና አጠቃቀምን በተመለከተ እስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ አመታዊ እቅድ ሊያዘጋጅ እና በየአመቱ የእቅድ ክንውን ሪፖርት በማዘጋጀት የታዩ የአፈፃፀም ክፍተቶች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን በሪፖርቱ ሊያካትት ይገባል፡፡

23. ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው ዓመታዊ ዕቅድ እና የእቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ የመንግስት የትርፍ ድርሻ አሰባሰብን የሚያካትት ሲሆን የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር አሰጣጥ፣ አሰባሰብ እና አጠቃቀምን በተመለከተ በእስትራቴጂክ እቅዱ ውስጥ የማያካትት በመሆኑ በየበጀት ዓመቱ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር የሚያገኙ

የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራትን በተቀመጠው መስፈርት መሠረት በመለየት ሊሰጥ ያቀደውን እና የሰጠውን የብድር ገንዘብ መጠን፣ ብድር የሚያገኙ አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶችን ብዛት እና የብድር አሰባሰብን እና አጠቃቀምን በተመለከተ እስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ አመታዊ እቅድና የእቅድ ክንውን ሪፖርት የማያዘጋጅ እንዲሁም በእቅድ ክንውን ሪፖርቱ ውስጥ የታዩ የአፈፃፀም ክፍተቶችን እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን የማያካትት መሆኑን ከተከለሱት ሰነዶች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

24. ስለ ሁኔታው የኤጀንሲው የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር የሚሰጣቸው ድርጅቶች ብዛትና የገንዘብ መጠን የሚወሰነው ከኤጀንሲው አልፎ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በአሁኑ አሰራር በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስለሆነ በኤጀንሲው ደረጃ በደንብ ቁጥር 107/1996 አንፃር በየዓመቱ የ40% እና 60% ድርሻን እያሰላ ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት የሚያሳውቅ መሆኑን ይህን መረጃ ማሳወቅ ደግሞ በእቅድ እንደተያዘ የገንዘብ መጠን እንደሚቆጠር ገልፀዋል፡፡

25. ይሁን እንጂ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብን በተመለከተ ኤጀንሲው ለአንድ የበጀት ዓመት ለልማት ድርጅቶች እንዲከፋፈል የሚያስፈልገውን ጥቅል የፈንድ መጠን ከትርፍ መጠን፣ከልማት ዓላማና ቅድሚያ ትኩረት እንደዚሁም ከልማት ድርጅቶቹ ፍላጎት ጋር ተገናዝቦ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቅረብ እንደሚገባው በኤጀንሲው በተዘጋጀው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም መመሪያ ላይ የተገለፀ ቢሆንም ተግባራዊ አላደረገውም፡፡ ይህም በመሆኑ በየበጀት ዓመቱ ለምን ያህል አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ብድር እንደሚሰጥ፣ ምን ያህል የገንዘብ መጠን እንደሚያበድርና ከዚህ ውስጥ ምን ያህል እንደሚሰበስብ በአመታዊ ዕቅዱ ውስጥ ባለማካተቱ ተግባራዊ ሲደረግ ስላጋጠሙ ችግሮች እና ሁኔታዎች፣ ስለተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች በእቅድ ክንውን ሪፖርቱ ባለማካተቱ ፈንዱ ለታለመለት አላማ ስለመዋሉና ስለአስገኘው ውጤት የተሟላ መረጃ ማግኘት አያስችልም፡

ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች እና አክስዮን ማህበራት የመንግስት ትርፍ ድርሻን ፈሰስ ማድረጋቸውን መከታተሉን በተመለከተ፣

26.ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች እና አክስዮን ማህበራት የሂሳብ አመቱ ካለቀ በኋላ ባሉት ስባት ወራት የመንግስት ትርፍ ድርሻ ፈሰስ እንዲያደርጉ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

27.ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችና አክስዮን ማህበራት በየበጀት አመቱ መክፈል ያለባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ ገቢ እንዲያደርጉ ደብዳቤ የሚጽፍ እና መርሃ ግብር/የጊዜ ሰሌዳ/ አዘጋጅቶ የሚልክ ቢሆንም 29 የመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክስዮን ማህበራት ፈሰስ ማድረግ የሚገባቸውን ብር 786,952,679 ገቢ ሳያድርጉ በአማካይ ከ2-3 አመት ያዘገዩ መሆኑን እንዲሁም እያንዳንዱ የልማት ድርጅትና አክሲዮን ማህበር የየበጀት ዓመት የትርፍ ድርሻ፣ ምን ያህል እንደተከፈለና ምን ያህል እንደቀረ ትንተና ለመስራት የሚያስችለውን የሂሳብ ቋት (ledger) ያላዘጋጀ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

28.ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የተጠራቀመ የመንግስት ትርፍ ድርሻ ብር 786,952,679 በተመለከተ በወቅቱ ያልተከፈለው ከ1995 በጀት ዓመት ጀምሮ ድርጅቶች ያተረፉትን ሙሉ በሙሉ ለመንግስት እንዲያስገቡ በመወሰኑ አብዛኞቹ ከስራ ማስኬጃ ችግርና የተወሰኑት ደግሞ ፕሮጀክት ጀምረው በወቅቱ ከተከሰተው የእቃዎች ዋጋ መናር ችግር ምክንያት ያለባቸው ሂሳብ ያልተሰበሰበ ሲሆን ይህም ከ2-3 ዓመት የዘለለ አለመሆኑን እንዲሁም በኤጀንሲው በኩል በየዓመቱ የዘመኑ እና ባለፈው ያልተከፈለውን በማጠቃለል እንዲከፍሉ ጥረት ቢደረግም ከላይ በተፈጠሩ ችግሮች ምክንያት ያልተከፈለ መሆኑን፣ የተወሰኑትም በተለያየ ጊዜ የአቅርቦት እጥረት ሲፈጠር በመንግስት ውሳኔ በራሳቸው ገንዘብ ገበያ እንዲያረጋጉ ስለሚደረግ መክፈል ያልቻሉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

29.ከትርፍ ድርሻ መረጃ ጋር ተያይዞ ለእያንዳንዱ የትርፍ ድርሻ የከፋይ ድርጅት የሂሳብ ቋት (ledger) መኖርን በተመለከተ በየዓመቱ በደንብ ቁጥር 107/96

መሰረት ድርጅቶች የሂሳብ መረጃቸውን እንዲልኩ ተደርጎ በቀጣይ በድራፍት የሂሳብ ሪፖርትና የውጭ ኦዲት ሪፖርት በየዓመቱ መጨረሻ ላይ ተጠቃሎ የሚያዝና በየበጀት ዓመቱ የየወሩ የተከፈለ የትርፍ ድርሻ መጠን በድርጅቱ ተደራጅቶ ከሂሳብ ማስታወቂያ ጋር ተመሳክሮና ታርቆ በሪፖርት መልክ ተዘጋጅቶ የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

30. ኤጀንሲው ከላይ የተጠቀሰውን የመንግስት የትርፍ ድርሻ ሂሳብ ከልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት በወቅቱ ወደ መንግስት ገቢ እንዲሆን ባለማድረጉ ሌሎች ችግር ያለባቸው ድርጅቶች እና አክሲዮን ማህበራት ገንዘቡን በብድር ወስደው ለልማት ተግባር ጥቅም ላይ እንዳያውሉት ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ እንዲሁም የእያንዳንዱን የልማት ድርጅትና አክሲዮን ማህበር የትርፍ ድርሻ ሂሳብ መከታተያ የሂሳብ ቋት (ledger) ያልተዘጋጀ በመሆኑ የየበጀት ዓመቱ የትርፍ ድርሻ ምን ያህል እንደተከፈለና ምን ያህል እንደቀረ የሚያስረዳ የሂሳብ ትንተና ለመስራት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

31. ይህንንም በተመለከተ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በመውጫ ስብሰባ ወቅት ካልተሰበሰበው የመንግስት ትርፍ ድርሻ ብር 786,952,679 ውስጥ የሙገር ሲሚንቶ ኢንተርፕራይዝ፣ ኮልፎስፌትና ጎማ ዛፍ ባንድ ላይ ሆነው የኬሚካል ኮርፖሬሽን እንዲቋቋም በመንግስት በመወሰኑ ከሙገር የሚጠበቀው የመንግስት ትርፍ ድርሻ ለድርጅቱ በpaid-up capital የተፈቀደለት በመሆኑ፣ አሰላ ብቅል ፋብሪካን በተመለከተ ማስፋፊያ ላይ የነበረ በመሆኑ የትርፍ ድርሻ ሂሳቡን በወቅቱ ገቢ ለማድረግ የስራ ማስኬጃ እጥረት ስለለሚኖርበት ገቢ ያላደረገ መሆኑን ከቀሪዎቹ ድርጅቶች የሚፈለገውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሂሳብ ለመሰብሰብ ጥረት እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

32. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው ባቀረበው ሰነድ ላይ የሙገር ሲሚንቶ ኢንተርፕራይዝ ያለበት የመንግስት ትርፍ ድርሻ ወደ paid-up capital እንዲዞር የተፈቀደለት መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ አላገኘንም፡፡

ኤጀንሲው ለመንግስት የልማት ድርጅቶች እና አክሲዮን ማህበራት በብድር የሰጠው ሂሳብ ውጤት ያስገኘ ስለመሆኑ መከታተሉን በተመለከተ፣

33. ኤጀንሲው ለመንግስት የልማት ድርጅቶች እና አክሲዮን ማህበራት በብድር የሰጠው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ ውጤት/ፋይዳ/ ያስገኘ መሆኑን ሊከታተል፣ ሊቆጣጠር እና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

34. ኤጀንሲው የመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የወሰዱት የብድር ሂሳብ ፋይዳ/ውጤት/ ያስገኘ ስለመሆኑ ከሚያቀርበው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም ሪፖርት በተጨማሪ የመስክ ጉብኝት/ምልከታ/ የሚያደርግ መሆኑን ቢገልፅም ይህንን በተመለከተ የተያዘ የመስክ ጉብኝት ሪፖርት አልቀረበም፡፡

35. የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው አክሲዮን ማህበራት የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ ብድር ለመውሰድ ባቀረበው የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ላይ ብድሩ ተፈቅዶለት ግንባታውን አጠናቆ ወደ ስራ በገባ በዓመቱ አትራፊ እንደሚሆን ያቀረበ ቢሆንም ብር 388,252,933 ፕሮጀክት ለማስፋፋት ወስዶ ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ወደ ስራ በገባ በአመቱ ብር 10,119,088 መክሰሩን፣ የኮስቲክ ሶዳ አክሲዮን ማህበር በ1995 ዓ.ም ብር 6,351,000፣ በ1999 ዓ.ም ብር 5,000,000 ብድር የወሰደ ቢሆንም አትርፎ የማያውቅ መሆኑን እንዲሁም የባቱ ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር በ1997 ዓ.ም ብር 12,440,000 ለማሽነሪና ተሽከርካሪዎች ግዥ ተበድሮ ግዥውን ፈፅሞ ወደ ስራ የገባ ቢሆንም አትራፊ ሊሆን ያልቻለ መሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

36. ይህንንም በተመለከተ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ለተሠጣቸው ድርጅቶች የተሰጠው ገንዘብ ያመጣው ፋይዳ/ውጤት/ ያስገኘ ስለመሆኑ ለብቻው የተዘጋጀ የመስክ ሪፖርት አለመኖሩን እንዲሁም ከኮስቲክ ሶዳ አክሲዮን ማህበር በስተቀር ሌሎቹ ከላይ የተጠቀሱት አክሲዮን ማህበራት ቀድሞ ፈንዱ ሳይሰጣቸው ያከማቹትን ኪሳራ እየቀነሱ መምጣታቸውን ገልፀዋል፡፡

37. የኦዲት ቡድኑ በናሙና መርጦ ላያቸው የአክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች እንዲሁም ለሌሎች ባለድርሻ አካላት የስራ ሃላፊዎች መጠይቅ በማቅረብና ማስረጃዎችን በመከለስ እንዳረጋገጠው አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የሚያቀርቡት የፕሮጀክት ጥናት በኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም መመሪያ መሰረት ኢኮኖሚያዊ፣ ፋይናንሻልና senesetivity አናሊስስ በጥልቀት አጥንተው የማያቀርቡ እንዲሁም ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የተበደሩትን ከብድሩ አላማ ውጪ የሚያውሉ መሆኑ በዚህም ምክንያት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የተበደሩትን ብድር በውላቸው መሰረት ተመላሽ የማያደርጉና አትራፊ መሆን ያልቻሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

38. ይህንንም በተመለከተ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት ከላይ የተገለፁት ድርጅቶች ብድሩን ከወሰዱ በኋላ አትራፊ ሆነው አለመገኘታቸውን ተቀብለው አትራፊ ያልሆኑበትን ምክንያት ሲያብራሩ ኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር በ2004 ዓ.ም ኤክስፖርት የሚያደርግበት ዋጋ በግማሽ የወረደ በመሆኑ፣ የአቅም አጠቃቀም፣ የሃይል መቆራረጥ፣ የማኔጅመንትና የጥጥ ጥራት ችግር መኖሩ አትራፊ እንዳላደረገው፣ ባቱ ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር ከማሽን ተከላ በኋላ ኪሳራ ላይ ቢሆንም ጥሩ ሁኔታ ላይ የነበረባቸው ዓመታትም እንደነበሩና አሁን ትርፍማ ወደ መሆን እየሄደ መሆኑን፣ ኮስቲክ ሶዳን በተመለከተ አክሲዮን ማህበሩ ማሽነሪዎችና መለዋወጫዎችን ገዝቶ ቴክኖሎጂ ሲመርጥ ችግር የነበረበት በመሆኑ አትራፊ መሆን አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

ኤጀንሲው የፀደቁ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የሚሰጡ ብድሮችን ለድርጅቶቹ ገቢ ማድረጉንና በወቅቱ ማሳወቁን በተመለከተ፣

39. ኤጀንሲው የፀደቁ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የሚሰጡ ብድሮችን ለየድርጅቶቹ በመርሀ-ግብሩ መሰረት ገቢ ሊያደርግና በወቅቱ ሊያሳውቃቸው ይገባል፡፡

40. ከ2002 በጀት ዓመት ጀምሮ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈንዱን ማስተዳደር ከጀመረ በኋላ እና በኤጀንሲው ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 730/2004 አንቀፅ

13 ንዑስ አንቀፅ 4 ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲያስተዳድር በመንግስት ከተወሰነ ወዲህ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ለተፈቀደላቸው አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች የተፈቀደላቸውን የፈንድ ብድር ሂሳብ በወቅቱ ወደ ባንክ ሂሳባቸው ገቢ በማድረግ የማያሳውቃቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

41. ስለ ሁኔታው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የስራ ሃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የኮልፎስፌት ማደበሪያ ኮምፕሌክስ ፕሮጀክት፣ ኢትዮጵያ ፐልፕና ወረቀት፣ ሃይድሮጅን ፐር ኦክሳይድና አዲስ ሴራሚክስ ብር 250.8 ሚሊየን ወደ ባንክ ሂሳባቸው ገቢ ከተደረገ በኋላ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተመልሶ የተወሰደባቸው በጊዜው የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ በርካታ ግዙፍ ኢንዱስትሪዎችን መያዝ የሚችሉ የኢንዱስትሪ ዞኖች ግንባታ ላይ በመሆኑና እነዚህ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቁ በመሆናቸው ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል ተብሎ በመታመኑ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

42. ይህንንም በተመለከተ ኤጀንሲውም ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ከተቋቋመ ከ1996 በጀት ዓመት ጀምሮ የተፈቀደ ገንዘብ በወቅቱ ወደ ተፈቀደላቸው ድርጅቶች የባንክ ሂሳብ ሲተላለፍ የቆየ ሲሆን ከ2002 በጀት ዓመት ጀምሮ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈንዱን ማስተዳደር በመጀመሩና በኋላም በ2004 በጀት ዓመት እንዲያስተዳድር በመንግስት በመወሰኑ ብድሩ ለተፈቀደላቸው ፕሮጀክቶች በወቅቱ ወደ ባንክ ሂሳባቸው ገቢ ማድረግ አለመቻሉ፣ ከላይ የተጠቀሱትን ፕሮጀክቶች በተመለከተ በኤጀንሲውና በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በተለያየ ጊዜ ቢጠየቅም ምላሽ ሊገኝ ያልቻለና እስካሁን የተለቀቀው 52 ሚሊየን ብቻ መሆኑ እንዲሁም የፕሮጀክቶች የ2005 በጀት አፈፃፀም ላይም ተመሳሳይ ተፅዕኖ ያመጣል የሚል ስጋት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

43. የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የፀደቀ ብድር በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኩል በወቅቱ ገቢ ይደረግ የነበረ መሆኑን፣ ነገር ግን ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከተላለፈ ጀምሮ ከ2-3 ወር ድረስ የሚዘገይ መሆኑን በዚህም ምክንያት የፕሮጀክት ግንባታ መዘግየት ላይ የራሱ ተፅዕኖ የፈጠረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

44. ይህንን በተመለከተ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የስራ ሃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በ2/8/2004 በቁጥር ሕ/ዳ/25 በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት ከ2004 በጀት ዓመት ግማሽ ዓመት በኋላ ስራው ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዛወረና ከዛ በፊት በኤጀንሲውና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ሲሰራ የነበረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከተዘዋወሩ በኋላ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ለተፈቀደላቸው አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች የተፈቀደላቸውን የፈንድ ብድር ሂሳብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ በማድረግ እንደማያሳውቃቸው የተጠቀሰውን በተመለከተ መልስ አልሰጡም፡፡

45.ኤጀንሲው፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አዲስ ለሚቋቋሙ፣ የማስፋፊያ ስራ ለሚሰሩ እና ለስራ ማስኬጃ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር በሚጠየቅበት ወቅት በአገር አቀፍ ደረጃ ለተያዙ አቅጣጫዎች ከፈንዱ ብድር መስጠት የሚቻለውን የገንዘብ አቅም ቀድመው በጋራ በጥልቀት መርምረው በጋራ አቋም ይዘው መወሰን ሲገባቸው ይህ ባለመሆኑ አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች የተፈቀደላቸውን የብድር ገንዘብ በመተማመን ስራ ከጀመሩ በኋላ ገንዘቡ በመርሃ-ግብራቸው መሰረት በወቅቱ ባለመለቀቁ ከፍተኛ የስራ መጓተት ሊፈጥርባቸው ችሏል፡፡

ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች የፈንድ አጠቃቀም ከታለመለት ዓላማ ውጭ ውሎ ሲያገኝ የማስተካከያ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን በተመለከተ፣

46.ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የሚወስዱት ብድር አጠቃቀም ከታለመለት አላማ ውጪ ሆኖ ሲያገኝ ምክንያቶችን በማጣራት ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ/እንዲወስድ/ ሊያደርግ ይገባል፡፡

47.የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በ20/08/95 ብር 22,264,000 እና በ15/09/97 ብር 3,965,697 በድምሩ ብር 26,229,697 የተበደረ ሲሆን ከዚህ ሂሳብ ውስጥ ብር 5,550,301 በፈንዱ ላልተፈቀደለት የማሽነሪ (pad roll bleaching) ግዥ፣ ብር 23,055 ለመደበኛ ስራ ማስኬጃና ብር 180,000 ላልተፈቀደ ግንባታ በድምሩ ብር 5,753,356 ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ

ወጪ ማድረጉ፣ በ2002 በጀት ዓመት ለኢንቨስትመንት ከተፈቀደለት ብር 5 ሚሊየን ውስጥ ብር 828,964 ከፈንዱ ዓላማ ውጭ ለስራ ማስኬጃ የተጠቀመ መሆኑን፣ ይህንንም በተመለከተ ኤጀንሲው ምክንያቱን በማጣራት አክሲዮን ማህበሩ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ያላደረገ መሆኑን ከተከለሱት ሰነዶች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

48. ከዚህም በተጨማሪ የኮስቲክ ሶዳ አክሲዮን ማህበር በ1995 በጀት ዓመት በድጋፍ ከተሰጠው ብር 6,351,000 ውስጥ ብር 3,900,000 ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የውል ስምምነት ውጭ ማዋሉ በውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት በመረጋገጡ አክሲዮን ማህበሩ በደብዳቤ ቁጥር ኮሶዳ/54/01 ነሐሴ 4/2001 ዓ.ም ለኤጀንሲው በፃፈው ደብዳቤ ከላይ የተገለፀውን የኦዲት ግኝት በተመለከተ ሂሳቡን የማጥራትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ ስራ በመስራት ላይ መሆኑን ገልጿል፡፡ ኤጀንሲውም በደብዳቤ ቁጥር መልድ 37-239/6/70 ነሐሴ 27/2002 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ከውል ስምምነት ውጭ የዋለው ብር 3.9 ሚሊየን ድርጅቱ ፈንዱን ለማንቀሳቀስ ወደ ከፈተው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የባንክ ሂሳብ ተመላሽ እንዲደረግ በደብዳቤ ያሳወቀ ቢሆንም ሂሳቡ ገቢ ስለመደረጉና የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ ማስረጃ አልተገኘም፡፡

49. የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበርን በተመለከተ የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በ1997 በጀት ዓመት ለማሽነሪ ግዥ ተከፍሎት ከነበረው ገንዘብ ላይ የተጠቀመ መሆኑን፣ ለተወሰነ ዓመት ከ1999-2000 ዓ.ም አክሲዮን ማህበሩ ለውጪ ባለሀብቶች በሊዝ በመሰጠቱ የፈንዱ አጠቃቀም በውጪ ኦዲተር በወቅቱ ኦዲት ባለመደረጉና ግኝቶቹን ለመከታተል ባለመቻሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

50. የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር የበላይ ሃላፊዎች ስለ ሁኔታ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አሁን ያለው ማኔጅመንት ባልነበረበት ጊዜ የተፈፀመና ማስረጃዎቹን ወደ ኋላ ዳሶ ማግኘት ያልቻሉ መሆኑና ወደ ፊት ስለ ሁኔታው አጣርተው ለኤጀንሲው ሪፖርት የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

51. የኮስቲክ ሶዳ አክሲዮን ማህበርን በተመለከተ የኤጀንሲው የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በኤጀንሲው በኩል ከውጭ ኦዲት ሪፖርቱ በመነሳት እንዲመለስ ክትትል የተደረገ ቢሆንም ድርጅቱ በከፍተኛ ችግር ውስጥ ያለና የስራ ማስኬጃ ችግር ያለበት ስለሆነ ወደ የፈንዱን ሂሳብ ማስመለስ አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

52. ኤጀንሲው ለልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ብድር ከሰጠ በኋላ ከወሰዱት አላማ ውጪ እንዳያውሉ የሚያደርገው ክትትልና ቁጥጥር የላላ መሆኑ ድርጅቶቹ ገንዘቡን ላልተፈቀደለት አላማ እንዲያውሉ መንገድ የሚከፍት በመሆኑ የፈንዱ ሂሳብ በወቅቱ ተመላሽ እንዳይደረግ ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች የፈንዱ ሂሳብ በየአመቱ በውጭ ኦዲተር እንዲያስመረምሩ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

53. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች የፈንድ ሂሳብ በየአመቱ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር እና በኦዲት ግኝቶች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡

54. በናሙና ከታዩት ድርጅቶች ውስጥ የሸቀጦች ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የወሰደውን ብድር በየአመቱ ያላስመረመረ መሆኑ፣ የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር እንደ አሮፓውያን አቆጣጠር በ2010 እና በ2011 በቀረበው የኦዲት ሪፖርት ላይ በድርጅቱ የሂሳብ መዝገብ እና በውጭ ኦዲተር ሪፖርት መካከል እንደ ቅደም ተከተሉ የብር 996,994 እና የብር 325,403 መንስኤው ያልተገለፀ ልዩነት (Unexplained difference) የተገኘ መሆኑ፣ እንዲሁም የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር የፈንዱን ሂሳብ በተለየ አካውንት የሚያስገባና የሚመዘግብ ቢሆንም በየበጀት ዓመቱ ሳያስመረምር የሁለት ዓመት ሂሳብ በአንድ ላይ ኦዲት ማስደረጉን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

55. ስለ ጉዳዩ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የሸቀጦች ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት ገንዘቡ የተሰጠው ለገበያ ማረጋጋት መሆኑና በድርጅቱ ኦፕሬሽን ውስጥ የተካተተ ስለሆነ ለብቻው ማስመርመር የማይጠበቅበት መሆኑን፣ ኮምቦልቻ ጨርቃ-ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ለተፈጠረው የሂሳብ ልዩነት ማስተካከያ

እንዲያደርጉ በኤጀንሲው በኩል በደብዳቤ ተጠይቀው የማስተካከያ መርሃ-ግብር ቀርቦ ክትትል እየተደረገ እንደሚገኝ እንዲሁም የባህርዳር ጨርቃ-ጨርቅ አክሲዮን ማህበር የሁለት ዓመት በአንድ ላይ ማስመርመሩ ለውጭ ኦዲተር የሚከፈለውን ወጪ ለመቆጠብና ፕሮጀክቱም ገና ስላልተጠናቀቀ አንድ ላይ መሆኑ የፕሮጀክቱን አፈፃፀም ለመገምገም አመቺ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

56. ሆኖም የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ውስጥ ለሸቀጦች ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት የስራ ሃላፊዎች ባቀረበው መጠይቅ፣ በሰጡት መልስና በተከለሱ ማስረጃዎች የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ በየበጀት ዓመቱ የማይመረመር መሆኑን፣ የኮምቦልቻ ጨርቃ-ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ባቀረበው የሂሳብ ማስተካከያ መርሃ ግብር ውስጥ ከላይ የተገለፁትን ግኝቶች አካቶ አለመገኘቱ እንዲሁም የባህርዳር ጨርቃ-ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም መመሪያ ውጭ የሁለት ዓመቱን ሂሳብ በአንድ ላይ ማስመርመሩ ታውቋል፡፡ ይህም በኦዲት ግኝቶች ላይ ወቅታዊ የሂሳብ ማስተካከያ እርምጃ እንዳይወስዱ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

ኤጀንሲው ለመንግስት ልማት ድርጅቶች ብድር በሚሰጥበት ጊዜ የብድር ውል ስምምነት የሚያስገባ መሆኑን በተመለከተ፣

57.ኤጀንሲው ለመንግስት ልማት ድርጅቶች ብድር በሚሰጥበት ጊዜ የብድር ውል ስምምነት እንዲገቡና በውሉ መሰረት የወሰዱትን ብድር ተመላሽ እንዲያደርጉ እንዲሁም በገቡት የውል ስምምነት መሰረት ካልፈፀሙ ውሉ እንዲቋረጥ ወይም የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡

58.የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት (ጅንአድ) ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በ8/7/2000 በወጪ ሰነድ ቁጥር ወ 084501 የወሰደውን ብድር ብር 50 ሚሊየን እስከ ጥቅምት 30/2002 ዓ.ም ለመመለስ ውል የገባ ቢሆንም ብድሩን በገባው ውል መሰረት ሳይመልስ ለሁለት አመት ያዘገየና ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስም ተመላሽ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ ስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ብድሩን ወቅታዊ ለሆነው የገበያ ማረጋጋት

ስራ እስከዛሬ ድረስ ተጠናክሮ የቀጠለ በመሆኑ በየጊዜው ተቆጣጣሪ ኤጀንሲውን እንዲያራዝመለት በመጠየቅ እየተጠቀሙበት በመሆኑ በውሉ ላይ በተቀመጠ የጊዜ ገደብ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

59.ባቱ ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በ17/2/97 በወጪ ሰነድ ቁ 01.66.21/33 የወሰደውን ብድር ብር 12,440,000 ለማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች መግዣ በሶስት አመት ለመመለስ ውል የገባ ቢሆንም በውሉ መሰረት ተመላሽ ሳያደርግ አራት አመት ያዘገየና ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ ተመላሽ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህንንም በተመለከተ የአክሲዮን ማህበሩ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ከፈንዱ የወሰዱትን ብድር ማህበሩ ኪሳራ ላይ በመሆኑ መመለስ አለመቻላቸውን ገልፀዋል፡፡

60.ኮስቲክ ሶዳ አክሲዮን ማህበር ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በተለያየ ጊዜ ከተበደረው ብር 22,928,358 ውስጥ ብር 3,666,666 በውሉ መሰረት በወቅቱ ተመላሽ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህንንም በተመለከተ የማህበሩ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በብደሩ የተገዙ ማሽነሪዎች ውጤት ሊያስገኙ ባለመቻላቸው ቀሪውን የብድር ገንዘብ ተመላሽ ያላደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

61.አዳሚ ቱሉ ፀረ-ተባይ ማዘጋጃ አክሲዮን ማህበር ከተበደረው ብድር ብር 12,126,503 ውስጥ ብር 3,031,625.75 የመመለሻ ጊዜው ያለፈ መሆኑ በኤጀንሲው የ2004 የአጠቃቀም ሪፖርት ላይ ተገልጿል፡፡ ይህንንም በተመለከተ የማህበሩ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ማህበሩ በገባው ውል መሰረት ተመላሽ ማድረግ ባለመቻሉ ኤጀንሲው በደብዳቤ መርሃ-ግብር አውጥቶ በየዓመቱ ገቢ እንዲያደርጉ ያሳወቃቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

62.የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር በተለያየ ጊዜ ከተፈቀደለት የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብር 388,252,933 ውስጥ ብር 35,369,185 እስከ ሰኔ 30/2004 ድረስ መከፈል የነበረበትና የመክፈያ ጊዜው ያለፈ ሲሆን የአክሲዮን ማህበሩ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ተመላሽ ያልተደረገበት ምክንየት አክሲዮን ማህበሩ በሙሉ አቅሙ ማምረት ባለመቻሉ፣ በተለያየ ጊዜ

የሃይል መቆራረጥ በመኖሩ፣ አገር አቀፍ የሆነ የግብአት ጥራት ችግር በመኖሩ እና የገንዘብ ምንዛሬ ለውጥ (devaluation) በመኖሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

63. ሐማሬሳ የምግብ ዘይት አክሲዮን ማህበር በ1998 ዓ.ም በወጭ ሰነድ ቁ. 560931 የተበደረውን 3 ሚሊየን እስከ ሐምሌ 2001 ተመላሽ ማድረግ የነበረበት መሆኑን፣ በ8/02/2000 በወጪ ሰነድ ቁ. 798709 የተበደረውን ብር 10,039,877 ከሐምሌ 2001-04 በየሶስት ወሩ እኩል ክፍያ እየከፈለ መመለስ የነበረበት ሲሆን ገንዘቡን በውሉ መሰረት ተመላሽ ሳያደርግ እንደቅደም ተከተላቸው 6 እና 4 ዓመት ያዘገየ እና ገቢ ያላደረገ መሆኑን፣አበቦ እርሻ ልማት ድርጅት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በ2000 ዓ.ም ከተበደረው ብር 38,290,144 ውስጥ ብር 16,316,057 ለ2 ዓመት ያህል ያዘገየና ገቢ ያላደረገ መሆኑን፣ እንዲሁም ሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በ1996 ዓ.ም በወጪ ሰነድ ቁ.15697 የተበደረውን ብር 884,000 በአንድ አመት መክፈል የነበረበት ሲሆን ለ7 ዓመት ያዘገየና ገቢ ያላደረገ መሆኑ ከ2004 ዓ.ም የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የአጠቃቀም ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

64. ከላይ የተገለፁት የልማት ድርጅቶች እና አክሲዮን ማህበራት በገቡት ውል መሰረት ገንዘቡን ተመላሽ እንዳላደረጉ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የሸቀጦች ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት በተመለከተ በኤጀንሲው በኩል በተደጋጋሚ እንዲከፍል ጥረት የተደረገና የደብዳቤ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በአገራችን የተከሰተውን የዘይትና የስኳር እጥረት እንዲያረጋጋ በመንግስት በመወሰኑና ለዚህም ስራ የኦፕሬሽን ወጪዎች የሚሸፈነው በድርጅቱ ስለሆነና ድርጅቱ የገንዘብ እጥረት ስለገመጠው የብድር መክፈያ ጊዜው እንዲራዘም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለኤጀንሲው ደብዳቤ በመፃፉ ያልተሰበሰበ መሆኑን፣ ባቱ ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር ከፈንዱ በብድር ተደግፎ መሳሪያዎች ቢገዛም በወቅቱ የተሰጠው ገንዘብ የድርጅቱን ችግር በሙሉ የሚቀርፍ ባለመሆኑ አፈፃፀሙም ስላልተሻሻለ በብድር ውሉ መሰረት መመለስ ያልቻለ መሆኑን፣ኮስቲክ ሶዳ አክሲዮን ማህበርን በተመለከተ ድርጅቱ ከፍተኛ የገንዘብ እጥረትና የተለያዩ ዕዳዎች ያሉበት በመሆኑ የተገዙ ማሽኖችን ለማንቀሳቀስ ተጨማሪ ገንዘብ በማስፈለጉ ዕዳው ሊሰበሰብ

አለመቻሉን፣ አዳሚ ቱሉ ፀረ-ተባይ አክሲዮን ማህበር የመመለሻ ጊዜው ያለፈበት መሆኑና እንዲከፍል በደብዳቤ የተጠየቀ መሆኑን፣ ኮምቦልቻ ጨርቃ -ጨርቅ አክሲዮን ማህበር መክፈል ያልቻለው ከፕሮጀክቱ መዘግየት ጋር ተያይዞ የተከሰተ ችግር ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ወደ ስራ ቢገባም ከመብራት መቆራረጥ ጋር በምርት ስራ ላይ ችግር ተፈጥሮ በሙሉ አቅሙ መስራት ባለመቻሉ መሆኑን፣ ሐማሬሳ የምግብ ዘይት አክሲዮን ማህበር ለጊዜው ገንዘብ ቢሰጠውም የተሰጠው ገንዘብ ዘላቂ ችግሩን የሚፈታ ባለመሆኑና አፈፃፀሙ ስላልተሻሻለ በውለታው መሰረት ሊከፈል አለመቻሉን፣ አበቦ እርሻ ልማት ድርጅት ባለፉት 3 ዓመታት በተፈጥሮአዊ የአየር መዛባት የተነሳ የታሰበውን ያህል ምርት ባለመገኘቱ ገንዘቡ ተመላሽ ሊደረግ አለመቻሉን፣ ሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅት በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ ድርጅቱ እርሻዎቹ በሙሉ በፕራይቬታይዜሽን ሂደት ወደ ግል ዞረው በጽ/ቤት ደረጃ ያለ ሲሆን በመንግስት ውሳኔ እንዲፈርስ ተደርጎ ዕዳው ለባለአደራ ቦርድ የሚተላለፍ እንጂ የሚሰበሰብ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

65. የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር በሚጠይቁበት ወቅት ፋይናንሻልና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት፣ sensitivity አናሊስስ እና ፕሮጀክቱ እንዳይሳካ ሊያደርጉ የሚችሉና ጥንቃቄ ሊወሰድባቸው የሚገቡ ሌሎች ጉዳዮች የሚያመጡትን ተፅዕኖ የሚያካትቱ የፕሮጀክት ጥናት ሰነዶች ማቅረብ እንደሚገባቸው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም መመሪያ ይገልፃል፡፡ ነገር ግን የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር በሚጠይቁበት ጊዜ የሚያቀርቡት የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ እነኝህን ጉዳዮች በጥልቀትና በተሟላ ሁኔታ ያላካተተ በመሆኑ ብድሩን ወስደው ውጤታማ ባለመሆናቸው የተበደሩትን ገንዘብ በገቡት ውል መሠረት ተመላሽ ማድረግ ያቅታቸዋል፡፡ ይህም በመሆኑ በገቡት ውል መሰረት ሳይመልሱ ከ2-6 ዓመት የዘገየ ብር 134,747,412 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

66. ከዚህም በተጨማሪ ኤጀንሲው ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የተሰጠውን ብድር ከውሉ ውጭ ማራዘም ያለበት መሆኑን የሚገልጽ መመሪያ ሳይኖር በኦዲቱ ወቅት ከታዩት ኮምቦልቻ ጨርቃ- ጨርቅ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የተበደረው 50,091,133.40 እስከ ሰኔ 30/2004 ማጠናቀቅ ሲገባው እስከ ሰኔ 30/2005 እንዲራዘምለት ማድረጉ፣

የሸቀጦች ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት የተበደረውን ብር 50 ሚሊየን ጥቅምት 30/2002 ዓ.ም አጠናቆ መክፈል ያለበት መሆኑ በውሉ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም በውላቸው መሰረት ተመላሽ ሳያደርግ እንዲራዘምለት አድርጓል፡፡

67. ይህንንም በተመለከተ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ኤጀንሲው የሚያስተዳድራቸው ድርጅቶችን በቅርቡ የሚከታተል በመሆኑ የሚደርስባቸው ችግር አሳማኝና ለማራዘም በቂ ሆኖ ከተገኘ እንዲራዘም እንደሚያደርግና በፈንድ ሪፖርቱ በማካተት ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንደሚያሳውቁ ገልፀዋል፡፡

68. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ወስደው በገቡት ውል መሰረት ተመላሽ ያላደረጉ የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት የወሰዱትን ብድር ኤጀንሲው እንዲያራዝምላቸው በሚጠይቁበት ወቅት ድርጅቶቹ የሚያቀርቧቸውን ምክንያቶች በመመርኮዝ ብቻ የሚያራዝምላቸው ሲሆን ኤጀንሲው መጋቢት 1995 ዓ.ም ባወጣው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም መመሪያ ላይ አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች የተበደሩትን የፈንድ ሂሳብ የሚራዘምላቸው ስለመሆኑ እና ለማራዘም የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ያልገለፀ በመሆኑ ድርጅቶቹ ሊራዘምላቸው የሚገባ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ ከመመሪያ/መስፈርት/ ጋር ማመሳከር አልተቻለም፡፡

ኤጀንሲው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ በሚዞሩበት ጊዜ ያለባቸውን የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድና የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሂሳብ እንዲከፍሉ ውል የሚያስገባ መሆኑን በተመለከተ፣

69. የመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ወደ ግል ይዞታ በሚዘዋወሩበት ጊዜ ያለባቸው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድና የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሂሳብ እንዲከፍሉ ውል ማስገባትና በውሉ መሰረት ገቢ እንዲያደርጉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

70. ኤጀንሲው በመንግስት ይዞታ ስር የነበሩ አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ወደ ግል በሚዛወሩበት ጊዜ በውጭ ኦዲተር አስመርምረው ያለባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ ገቢ እንዲያደርጉ ውል ያስገባ ቢሆንም ከሐረር ቢራ አክሲዮን ማህበር 8,362,019፣ ከአምቦ ማዕድን ውሃ 7,806,125፣ ከቦሌ ቡልቡላ ኮንስትራክሽን

2,381,490 በድምሩ ብር 18,549,634 የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሂሳብ ገቢ ያልተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

71. ይህንንም በተመለከተ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ወደ ግል ከተዘዋወሩ አክሲዮን ማህበራት የሚፈለገው ብር 18,549,634 በተመለከተ ኤጀንሲው እንዲከፍሉ ጥረት እያደረገ መሆኑን፣ የአምቦ ማዕድን ውሃ አክሲዮን ማህበር በተመለከተ ክፍያው የባለአክሲዮኖች ስብሰባ ተደርጎ የሚወሰን እንጂ ያልተሰበሰበ የትርፍ ድርሻ ሂሳብ አለመሆኑን ቀሪዎቹ ማለትም (ሐረር ቢራ አክሲዮን ማህበርና ቦሌ ቡልቡላ ኮንስትራክሽን) እንዲከፍሉ ደብዳቤ ተፅፎላቸው የቅርብ ክትትል እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

72. በኦዲቱ ከተከለሰው ማስረጃ ለማወቅ እንደተቻለው ከአምቦ ማዕድን ውሃ አክሲዮን ማህበር የሚፈለገው ብር 7,806,125 ኤጀንሲው ወደ ግል ከተዛወሩ አክሲዮን ማህበራት የመንግስት ትርፍ ድርሻ ተሰብሳቢ ሂሳብ የያዘው መሆኑ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች በገቡት ውል መሰረት በውጭ ኦዲተር አስመርምረው ያለባቸውን የትርፍ ድርሻ ሂሳብ ገቢ ባለማድረጋቸው ከትርፍ ድርሻ ሂሳብ መንግስት ተፈፃሚ ለማድረግ ያቀዳቸውን ተግባራት እንዳያሳካ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

73. ኤጀንሲው በመንግስት ይዞታ ስር የነበሩ አክሲዩን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ወደ ግል በሚዛወሩበት ጊዜ ያለባቸውን የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ገዢ ባለሀብቶቹ እንዲከፍሉ ውል ያስገባ ቢሆንም አርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ብር 10,191,787፣ የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት ብር 11,976,098፣ታቦር ሴራሚክ ውጤቶች አክሲዮን ማህበር ብር 6,220,831 ፣የኢትዮጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር ብር 11,780,500 ፣የሃዋሳ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ብር 4,084,825 በድምሩ ብር 44,254,041 ገዢ ባለሀብቶች በገቡት ውል መሰረት ያለባቸውን የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ተመላሽ አላደረጉም፡፡

74. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅና ታቦር ሴራሚክ ውጤቶች አክሲዮን ማህበር እንዲከፍሉ ደብዳቤ ተፅፎ ክትትል እየተደረገ መሆኑን፣ የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት

እንዲከፍል በተደጋጋሚ ደብዳቤ ተፅፎለት ፍቃደኛ ባለመሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተያዘ መሆኑን፣ ኢትየጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር እንዲከፍል ክትትል ተደርጎ በአሁኑ ጊዜ በየወሩ ብር 500,000 እየከፈለ ቢሆንም በሙሉ አጠናቆ እንዲከፍል በደብዳቤ ተጠይቆ ባለሀብቱ ጉዳዩን በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኩል እንዲታይለት በደብዳቤ ጠይቆ ውጤት እየተጠበቀ መሆኑን፣ በኤጀንሲው በኩል ግን ከውጤቱ በኂላ ወደ ፍርድ ቤት ለመላክ በዝግጅት ላይ መሆኑን እንዲሁም ሃዋሳ ጨርቃ ጨርቅ የውል ማሻሻያ የተደረገበትና የመክፈያ ጊዜ እንዲራዘም የተደረገ በመሆኑ ጊዜው ያለፈበት አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

75. የሃዋሳ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበርን በተመለከተ ኤጀንሲውና ድርጅቱን የገዛው አክሲዮን ማህበር በገቡት ውል ውስጥ ብር 20,424,129 የሽያጭ ውል ከተፈረመበት መጋቢት 26/2003 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ተከታታይ አምስት ዓመታት ውስጥ በእኩል ዓመታዊ ክፍያ ገዢ ለሻጭ መክፈል አለበት የሚል በመሆኑ ብር 4,084,825 የመክፈያ ጊዜው ያለፈበት መሆኑ ታውቋል፡፡

76. ከዚህም በተጨማሪ በመንግስት ይዞታ ስር በነበሩበት ጊዜ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር የተሰጣቸውና ሳይከፍሉ በፕራይቬታይዜሽን ሂደት ወደ መንግስትና ወደ ግል በመዞራቸው ዕዳው ወደ መንግስት ልማት ድርጅት ባለአደራ ቦርድ የተላለፈባቸው (አደይ አበባ ድርና ማግ ብር 44,339,696፣ አዲስ አበባ ፎምና ፕላስቲክ ፋብሪካ ብር 5,333,331፣ ኢትዮጵያ ቃጫ ፋብሪካ ብር 2,500,000፣ ቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ 30,000,000፣ ድሬዳዋ ጨርቃ-ጨርቅ ፋብሪካ ብር 7,000,000፣ ጥቁር አባይ ኮንስትራክሽን ብር 14,713,601) በድምሩ ብር 103,886,628 ያልተመለሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

77. በፕራይቬታይዜሽን ሂደት ወደ መንግስትና ግል በመዛወራቸው ዕዳው ወደ መንግስት ልማት ድርጅት ባለአደራ ቦርድ የተላለፈውን ብር 103,886,628 በተመለከተ የባለአደራ ቦርዱ ዋና ዳይሬክተር ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ድርጅቶች ሲሸጡ በርክክብ መዝጊያ ዕለት ያለ ሃብትና ዕዳ ሂሳብ በመዝጋት እንደሚሰራ

ተከፋይ የሚያስተናግዱት ጠያቂ ሲቀርብ ብቻ መሆኑን እስካሁን ከላይ የተገለፁትን ድርጅቶች በተመለከተ የተጠየቀም የተከፈለም አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

78. በዚህ ዙሪያ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በፕራይቬታይዜሽን ሂደት ወደ ግል ተዛውረው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ዕዳቸው ወደ ባለአደራ ቦርድ የተላለፉ ብር 103,886,628 በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 146/1991 እና በኤጀንሲው የድርጅቱ የሽያጭ መመሪያ ድርጅቶች/ፋብሪካዎች/ኢንተርፕራይዞች/ ወደ ግል ሲዛወሩ ሃብትና ዕዳውን የሚረከበው የመንግስት ልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ስለሆነና የተጠቀሱት ድርጅቶችም ሲረካከቡ የባለአደራ ቦርዱ ባለሙያዎች በቦታው ተገኝተው የሰነድ ርክክብ ስለሚያደርጉ ሂሳቡን አዘግተውና በውጭ ኦዲተር አስመርምረው ዕዳውን ለመንግስት እንዲያስገቡ በአዋጅ ስልጣን የተሰጠው ለባለአደራ ቦርዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

79. ኤጀንሲው ወደ ባለአደራ ቦርድ የተላለፉ ድርጅቶች/አክሲዮን ማህበራት/ ፋብሪካዎች እና ኢንተርፕራይዞች ሂሳባቸውን በሰነድ ርክክብ ወቅት እንዲያውቀው የሚደረግ ሲሆን የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ያለባቸው ድርጅቶች ሂሳብ ባለአደራ ቦርዱ ሂሳቡን ተከታትሎ ገቢ እንዲያደርጉ ባለማድረጉ ከላይ የተገለፀው ሂሳብ ገቢ ሳይሆን ተገኝቷል፡፡

80. ከዚህም ሌላ በኢትዮጵያ መንግስትና ሳይገን ግሩፕ በተባለ የቱርክ ባለሀብቶች ሳይገን ዲማ ጨርቃ-ጨርቅ አክሲዮን ማህበርን ለመመስረት በ2003 ዓ.ም ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የመንግስት ድርሻ ሂሳብ በሚከፈልበት ጊዜ 327,107.8 USD በብልጫ የተከፈለና ያልተመለሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

81. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በኢትዮጵያ መንግስትና ሳይገን ግሩፕ በተባለ የቱርክ ባለሀብቶች ከፈንዱ በብልጫ የተከፈለው የመንግስት ድርሻ ሂሳብ 327,107.8 USD በኤጀንሲው በኩል ለፕሮጀክቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ በደብዳቤ የተገለፀላቸው መሆኑና ፕሮጀክቱ ያልተጠናቀቀና ወደ

ስራ ያልገባ መሆኑን፣ ስራውን ሲጀምር የባለአክሲዮኖች ስብሰባ ተደርጎ ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

82. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ እንደተቻለው አክሲዮን ማህበሩ የፕሮጀክት ስራውን አጠናቆ ወደ ትግበራ የገባ መሆኑና በብልጫ ለአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለውን የመንግስት ድርሻ ሂሳብ ኤጀንሲው ተከታትሎ ወደ መንግስት ተመላሽ እንዲደረግ ወይም በተጨማሪ ድርሻነት እንዲመዘገብ ያለመደረጉ ታውቋል፡፡

ለ. የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አዋጆችን ፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን ተፈጻሚ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የሚሰሩበት ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርአት የተዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

የፈንድ አጠቃቀም ግምገማ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣

83. ኤጀንሲው የየድርጅቶቹ ዋና ስራ አስኪያጆችና የቦርድ ሰብሳቢዎች በተገኙበት የፈንድ አጠቃቀም ግምገማ በአመት ሁለት ጊዜ ሊያካሂድ ይገባል፡፡

84. ኤጀንሲው የየድርጅቶቹ ዋና ስራ አስኪያጆችና የቦርድ ሰብሳቢዎች በተገኙበት የፈንድ አጠቃቀም ግምገም በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ የሚያደርግ መሆኑን ቢገልፅም ከ2001-04 ባለው ጊዜ ውስጥ የፈንድ አጠቃቀም ግምገማ ሲደረግ የተያዘ ቃለ-ጉባኤ እንዲቀርብልን ጠይቀን የቀረበው በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ተሰጥቷቸው ክፍያውን በወቅቱ ካልከፈሉ ድርጅቶች ጋር የተደረገ ስብሰባ አንድ ቃለ ጉባኤ ብቻ ነው፡፡

85. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት ድርጅቶች የአዳሚ ቱሉ ፀረ-ተባይ፣የኮስቲክ ሶዳ፣የኮምቦልቻ ጨርቃ-ጨርቅና የባህርዳር ጨርቃ-ጨርቅ አክሲዮን ማህበር የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው የፈንድ አጠቃቀም ግምገማ በተመለከተ ውይይት የሚያደርጉ መሆኑን ነገር ግን በአመት ሁለት ጊዜ በመደበኛነት የማይሰበሰቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

86. ይህንንም በተመለከተ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በፈንድ አጠቃቀም ዙሪያ በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ ሳይሆን እንደአስፈላጊነቱ ከሁለት

ጊዜ በላይ ከሌሎች የውይይት አጀንዳዎች ጋር ተያይዞ ውይይት እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

87. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት የፈንድ አጠቃቀም ግምገማ የአክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች የስራ ሃላፊዎች በተገኙበት ከ2001-04 በዓመት ሁለት ጊዜ መደረጉን የሚያሳይ ማስረጃ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ የቀረበው ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ተሰጥታቸው ክፍያውን በወቅቱ ያልከፈሉ ጋር የተደረገ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ 1 ብቻ ነው፡፡ ይህ ስብሰባ ወቅቱን ጠብቆ በአመት ሁለት ጊዜ በየስድስት ወሩ ያለመደረጉ በኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም ዙሪያ የተከሰቱ ችግሮችን በወቅቱ ተረድቶ ችግሮቹን ለማቃለል የሚረዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን በወቅቱ ለመውሰድ አያስችልም፡፡

88. ይህንንም በተመለከተ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት የፈንድ አጠቃቀም ግምገማን በተመለከተ በትክክል በዓመት ሁለት ጊዜ እንደማያደርጉ፣ ስብሰባ በሚደረግበት ወቅትም ቃለ-ጉባኤ የመያዝ ልምድ የሌላቸው መሆኑን ወደ ፊት ግን ለመያዝ ጥሩ ማሳሰቢያ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ክፍል ሦስት#

የመደምደሚያ ሃሳቦች

89.የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አሰባሰብና አጠቃቀም ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ እንዲሆን የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን፡፡ እነዚህ ጥረቶች መደረጋቸው የሚበረታታና የሚደገፍ ቢሆንም የአሰራር ስርአቱ አፈፃፀምና ውጤታማነት በኦዲቱ በሚገመገምበት ወቅት ከዚህ በታች የተመለከቱ ዋና ዋና የአሠራር ግድፈቶች ያሉበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

- ኤጀንሲው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድርን በተመለከተ ስትራቴጂክ እቅዱ ውስጥ ያላካተተ እንዲሁም ስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ አመታዊ እቅድ ያላቀደ፣ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ያላዘጋጀና የታዩ የአፈፃፀም ክፍተቶችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ያላካተተ በመሆኑ በየበጀት ዓመቱ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሊሰጥ ያቀደውን ብድርና የተከናወነውን፣ ተጠቃሚ ለማድረግ ያቀደውን የአክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ብዛት፣ በበጀት ዓመቱ ለመሰብሰብ የታቀደውንና የተሰበሰበውን የብድር ተመላሽ ሂሳብ እና በየጊዜው የገጠሙ የአፈፃፀም ክፍተቶችን እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ለማወቅና ውጤታማነቱን ለመመዘን አለማስቻሉ፣

- የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት በደንቡ መሰረት የመንግስት ትርፍ ድርሻ ፈሰስ ማድረግ ሲገባቸው ብር 786,952,679 ገቢ ሳያደርጉ ከ2-3 ዓመት የዘገየ መሆኑ እንዲሁም የእያንዳንዱ የልማት ድርጅትና አክሲዮን ማህበር የየበጀት ዓመት የትርፍ ድርሻ ምን ያህል እንደተከፈለና ምን ያህል እንደቀረ ትንተና ለመስራት የሚያስችል የሂሳብ ቋት (ledger) ያላዘጋጀ መሆኑ፣

- ኤጀንሲው ለልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት በብድር የተሰጠው ሂሳብ ውጤት ወይም ፋይዳ ያስገኘ መሆኑን የማይከታተል መሆኑ፣

- የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ለፀደቀላቸው ድርጅቶች ኤጀንሲው በወቅቱ ወደ አካውንታቸው ሂሳቡን ገቢ አድርጎ የማያሳውቃቸው አለመሆኑ፣

- ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት የፈንድ አጠቃቀም ከታለመለት አላማ ውጭ ሆኖ ሲያገኘው ምክንያቶችን በማጣራት ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያደርገው ክትትልና ቁጥጥር የላላ መሆኑ፣

- ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ወስደው በገቡት ውል መሰረት ብድሩን ተመላሽ ካላደረጉ የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ብር 134,747,412 ያልተሰበሰበ መሆኑ እንዲሁም ኤጀንሲው የብድር ማራዘሚያ መመሪያ ወይም መስፈርት ሳይኖረው አክሲዮን ማህበራቱና የልማት ድርጅቶቹ በሚያቀርቡት ምክንያት በመመርኮዝ ብር 100,091,133.40 የመክፈያ ጊዜ እዲራዘምላቸው ማድረጉ፣

- ኤጀንሲው ወደ ግል ይዞታ ከተዛወሩ 3 የልማት ድርጅቶች ብር 18,549,634 የመንግስት የትርፍ ድርሻ ፣ ወደ ግል ይዞታ ከዞሩ 5 የልማት ድርጅቶች ብር 44,254,041 የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ እንዲሁም በፕራይቬታይዜሽን ሂደት ወደ መንግስትና ወደ ግል በመዛወራቸው ዕዳው ወደ ባለአደራ ቦርዱ ከተላለፉ 6 ፋብሪካዎች ብር 103,886,628 የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በድምሩ ብር 166,690,303 ሂሳብ አለመሰብሰቡ እንዲሁም በኢትዮጵያ መንግስትና ሳይገን ግሩፕ በተባለ የቱርክ ባለሀብቶች ሳይገን ዲማ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበርን ለመመስረት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በሚከፈልበት ጊዜ የመንግስት ድርሻ 327,107.8 USD በብልጫ የተከፈለና ለመንግስት ያልተመለሰ መሆኑ፣

- ኤጀንሲው በፈንድ አጠቃቀም መመሪያው መሰረት ከአክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች ጋር በኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም ላይ በዓመት ሁለት ጊዜ የፈንድ አጠቃቀም ግምገማ የማያደርግ መሆኑ፣

የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሂሳብ አሰባሰብ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ ብድር አሰጣጥ፣ አጠቃቀም እና አሰባሰብ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ ስለሆነም በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን

የአሰራር ግድፈቶች እና ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

90. ኤጀንሲው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ፕሮግራምን ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲያስችለው የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራትን የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ፍላጎት ጥናት በማድረግ የሚሰጠውን የብድር መጠን፣ ብድሩን የሚያገኙ የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ብዛትና የሚሰበስበውን የፈንድ ሂሳብ የብድር ተመላሽ መጠን እና የሚሰበሰብበትን ጊዜ በስትራቴጂክ እቅድ ውስጥ ሊያካትት እና ይህንኑ መሰረት በማድረግ አመታዊ እቅድ ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊነቱን ሊያረጋግጥ እንዲሁም በዕቅድ ክንውን ሪፖርቱ ውስጥ ለታዩ የአፈፃፀም ክፍተቶች የመፍትሄ እርምጃ መወሰዱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

91. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት መክፈል የሚገባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ገቢ እንዲያደርጉ ክትትል ሊያደርግና ሂሳባቸውን በወቅቱና በትክክለኛው መጠን ገቢ ማድረጋቸውን ለመከታተል የሚያስችል የሂሳብ ቋት (ledger) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

92. ኤጀንሲው የመንግስት የልማት ድርጅቶና አክሲዮን ማህበራት ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የወሰዱት ብድር ውጤት/ፋይዳ ያስገኘ መሆኑን የልማት ድርጅቶቹ ከሚያቀርቡት የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም ሪፖርት በተጨማሪ የመስክ ምልከታ በማድረግ ሊከታተልና ሊቆጣጠር እንዲሁም በመስክ ምልከታ ወቅት ለታዩ የአፈፃፀም ክፍተቶች የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን አካቶ የመስክ ጉብኝት ሪፖርት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

93. ኤጀንሲው ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ዓላማ እና በአገር አቀፍ ደረጃ ካላቸው ፋይዳ አንፃር የፕሮጀክት ግንባታና ማስፋፊያ ለማድረግ ጥናት አቅርበው የተፈቀደላቸው አክሲዮን ማህበራትና የልማት ድርጅቶች በፕሮጀክት ጥናታቸው መርሃ-ግብር

መሰረት የፈንድ ሂሳቡ ገቢ እንዲደረግላቸው ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር የፈንድ ሂሳቡ በወቅቱ ገቢ እንዲደረግላቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡

94. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችንና አክሲዮን ማህበራት በየበጀት ዓመቱ ሂሳባቸውን በውጭ ኦዲተር እንዲያስመረምሩና በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ ለታለመለት አላማ ብቻ እንዲውል ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ እንዲሁም ከታለመለት አላማ ውጭ ውሎ ሲያገኝ ምክንያቶችን በማጣራት ወቅታዊ እርምጃ ሊወስድ/እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡

95. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት የወሰዱትን ብድር በገቡት ውል መሰረት ተመላሽ እንዲያደርጉ የሚያቀርቧቸውን የፕሮጀክት ጥናቶች አዋጭነት ከኢኮኖሚያዊ፣ ከፋይናንሻልና sensetivity አናሊስስ አንፃር ጭማሪ በጥልቀት በመመርመር ብድራቸውን ተመላሽ ሊያደርጉ የሚችሉ መሆኑን ሊያረጋግጥ እንዲሁም በወቅቱ ብድራቸውን በገቡት ውል መሰረት ተመላሽ ለማድረግ ካልቻሉ ውሉ እንዲቋረጥ/የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡

96. ኤጀንሲው በፕራይቬታይዜሽን ሂደት ወደ ግል ይዞታ የሚዛወሩ የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ያለባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ እንዲከፍሉ ውል ሊያስገባ እና በውሉ መሰረት ገቢ እንዲያደርጉ ከባለአደራ ቦርድ እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ፣ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

97. ኤጀንሲው በኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም መመሪያ መሰረት የልማት ድርጅቶችና የአክሲዮን ማህበራት ዋና ስራ አስኪያጆችና የቦርድ ሰብሳቢዎች በተገኙበት በአመት ሁለት ጊዜ የፈንድ አጠቃቀም ግምገማ ሊያካሂድ፣

የግምገማውን ቃለ-ጉባኤዎች አሟልቶ ሊይዝ እና በውይይቶቹ ላይ ለሚነሱ ችግሮች የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ለኦዲቱ መረጃ የሰበሰብንባቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ድርጅቶች፣ አክሲዮን ማህበራት፣ ፋብሪካዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የስራ ሃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የስራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪዎች

አባሪ 1

<u>የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች</u>

የኦዲቱ ጭብጥ (Audit Issues)	መስፈርቶች (Evaluative Criteria's)
1. የመንግስት የትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ አሰባሰብና አጠቃቀምን በተመለከተ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዐት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣	
1.3 ኤጀንሲው ከመንግስት ልማት ድርጅቶች እና አክሲዮን ማህበራት በየበጀት ዓመቱ የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብን በወቅቱ ለመሰብሰብ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ እና ቀልጣፋ የአሰራር፣ የቁጥጥር እና የክትትል ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣	1. ኤጀንሲው የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ አሰባሰብ እና አጠቃቀምን በተመለከተ ግልፅ መመሪያ ሊያዘጋጅና ለየልማት ድርጅቶቹ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡
	2. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች የመንግስት ትርፍ ድርሻና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ አሰባሰብና አጠቃቀም ባወጣው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ማድረጋቸውን መከታተል ይገባዋል፡፡
	3. ኤጀንሲው የመንግስት ትርፍ ድርሻ አሰባሰብን እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ሂሳብ አሰባሰብ፣ ብድር አሰጣጥና አጠቃቀም በተመለከተ የሚያከናውነውን ተግባር የስትራቴጂክ እቅድ ውስጥ ሊያካትት ይገባል፡፡

የኦዲቱ ጭብጥ (Audit Issues)	መስፈርቶች (Evaluative Criteria's)
	4. ኤጀንሲው ባዘጋጀው ስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት የመንግስት ትርፍ ድርሻ አሰባሰብና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር አሰጣጥ፣አጠቃቀምን በአመታዊ እቅድ ውስጥ በማካተት በእቅዱ መሰረት ተግባራዊ መደረጋቸውን በየአመቱ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
	5. ኤጀንሲው የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር አሰጣጥና አሰባሰብን በተመለከተ ስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ አመታዊ እቅድ ሊያቅድና እና የእቅድ ክንውን ሪፖርት በየአመቱ ሊያዘጋጅ እና የታዩ የአፈፃፀም ክፍተቶች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርጃዎችን ሊያካትት ይገባል፡፡
1.4 ኤጀንሲው የመንግስት የትርፍ ድርሻ ሂሳብ አመዘጋገብ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድን ለልማት ድርጅቶች እና አክሲዮን ማህበራት የሚሰጥበትን የብድር አሰጣጥ፣ አመዘጋገብ፣ አጠቃቀም እና አመላለስን ውጤታማ ማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱ እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣	6. ኤጀንሲው ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ተጠቃሚ የሚሆኑ የልማት ድርጅቶች የሚመረጡበትን ዝርዝር ምክንያት/መስፈርት ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡

የኦዲቱ ጭብጥ (Audit Issues)	መስፈርቶች (Evaluative Criteria's)
	7. ኤጀንሲው የመንግስት የልማት ድርጅቶች በየበጀት ዓመቱ የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሂሳብን የሚያሳውቁበት እና ገቢ የሚያደርጉበት የጊዜ ሰሌዳ ሊያዘጋጅ፣ ሊያሰራጭ እና ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተል ይገባል፡፡
	8. ኤጀንሲው የመንግስት ልማት ድርጅቶች በሚያቀርቡት ጊዜያዊ የሂሳብ መግለጫ ላይ ተመስርቶ በበጀት ዓመቱ የተገኘውን የተጣራ ትርፍ በጀት ዓመቱ ካለቀ እስከ ህዳር 15 ለኢንዱስትሪ ሚ/ር ሊያሳውቅ ይገባል፡፡
	9. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች/አክስዮን ማህበራት የሂሳብ አመቱ ከተፈጸመ ጊዜ አንስቶ ባሉት ስባት ወራት የመንግስት ትርፍ ድርሻ ፈሰስ እንዲያደርጉ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
	10. ኤጀንሲው ለመንግስት የልማት ድርጅቶች በብድር/ድጋፍ የሰጠው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ውጤት/ፋይዳ ያስገኘ ስለመሆኑ ሊከታተል፣ ሊቆጣጠር እና ሊያረጋግጥ ይገባዋል፡፡
	11. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች በፈንዱ አጠቃቀም ማኔጅመንቱ ወይም ቦርዱ ሃላፊነታቸውን ካለመወጣት በተጨማሪ ብክነት ወይም ሙስና እንዲከሰት ካደረጉ

የኦዲቱ ጭብጥ (Audit Issues)	መስፈርቶች (Evaluative Criteria's)
	ኦዲተር መድቦ እንዲጣራ በውጤቱም መሰረት ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	12. ኤጀንሲው የፀደቁ የፈንድ ድጋፎች/ብድሮችን ለድርጅቶቹ ገቢ ሊያደርግና በወቅቱ ሊያሳውቃቸው ይገባል፡፡
	13. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች የፈንድ አጠቃቀም ከታለመለት አላማ ውጪ ሆኖ ሲገኝ ምክንያቶችን በማጣራት ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ/እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	14. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች የፈንድ ሂሳብ በየአመቱ በውጭ ኦዲተር እንዲያስመረምሩ እና በኦዲት ግኝቶች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	15. የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሂሳባቸውን በውጪ ኦዲተር ሲያስመረምሩ የተመደቡትን ኦዲተሮች ኤጀንሲው ሊያፀድቅ ይገባል፡፡
	16. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች በውጭ ኦዲተር ያስመረመሩትን የፈንድ ሂሳብ ሪፖርት በየአመቱ እንዲያቀርቡ ሊያደርግና ለኢንዱስትሪ ሚ/ር ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

የኦዲቱ ጭብጥ (Audit Issues)	መስፈርቶች (Evaluative Criteria's)
	17. ኤጀንሲው ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚሰጠው ድጋፍ/ብድር በኢንዱስትሪ ሚ/ር ሊፈቀድ ይገባል፡፡
	18. ኤጀንሲው ለመንግስት ልማት ድርጅቶች ብድር በሚሰጥ ጊዜ የብድር ጥያቄው ፈንዱ ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር የተገናኘ ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
	19. የመንግስት የልማት ድርጅቶች የፈንድ ፍላጎት ጥያቄአቸውን በሥራ አመራር ቦርድ አማካይነት ለኤጀንሲው በፅሁፍ ከፕሮጀክት ሰነድ/ጥናት ጋር ሊያቀርብ ይገባል፡፡
	20. ኤጀንሲው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ከመዝገብ ስለሚሰረዝበት ሁኔታ መመሪያ ሊያወጣ እና አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** አዋጅ ቁ.412/96
	21. ኤጀንሲው ለመንግስት ልማት ድርጅቶች ብድር በሚሰጥ ጊዜ የብድር ውል ስምምነት እንዲገቡና በውሉ መሰረት ተመላሽ እንዲያደርጉ ሊያደርግ ይገባል፡፡፡ **ምንጭ፡- የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አጠቃቀም መመሪያ ገፅ** 8 **ተራ.ቁ** 6
	22. ኤጀንሲው የመንግስት ልማት ድርጅቶች ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የሚያገኙትን ብድር በገቡት የውል ስምምነት መሰረት

የኦዲቱ ጭብጥ (Audit Issues)	መስፈርቶች (Evaluative Criteria's)
	ካልፈፀሙ ውሉ እንዲቋረጥ/የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	23. የመንግስት የልማት ድርጅቶችና ኢ.ማህበራት በኤጀንሲውና በባለአደራ ቦርድ በኩል ወደ ግል ይዞታ በሚዘዋወሩ ጊዜ ያለባቸው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድና የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሂሳብ እንዲከፍሉ ውል ማስገባትና በውሉ መሰረት ገቢ እንዲያደርጉ ሊደረግ ይገባል፡፡
	24. ኤጀንሲው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የተፈቀደላቸው የመንግስት ልማት ድርጅቶች የፈንዱን አጠቃቀም ዝርዝር እና መጠን የሚያሳይ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡
2. የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ አዋጆችን ፤ ደንቦች እና መመሪያዎችን ተፈጻሚ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የሚሰሩበት የአሰራር ስርዐት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርአት የተዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፡፡	
2.1 ኤጀንሲው ከኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር፣ ከመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ አክሲዮን ማህበራት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ የመወያያ መድረክ፣ ዕቅድ እና የዕቅድ ክንውን ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣	25. ኤጀንሲው ከገኢ/ሚ/ር፣ ከመንግስት የልማት ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ የሆነ አሰራር ሊኖረው ይገባል፡፡
	26. ኤጀንሲው የፈንድ አጠቃቀም ግምገማ የድርጅቶቹ ዋና ስራ አስኪያጆችና የቦርድ ስብሳቢዎች በተገኙበት በአመት ሁለት ጊዜ

የኦዲቱ ጭብጥ (Audit Issues)	መስፈርቶች (Evaluative Criteria's)
	ሊያካሂድ ይገባል፡፡
	27. ኤጀንሲው ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር የተሰጣቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች በየበጀት ዓመቱ የፈንዱን አጠቃቀም የሚያሳይ እቅድና የእቅድ ክንውን ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	28. ኤጀንሲው የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ዓመታዊ የትርፍ ድርሻ ክፍያን የሚያሳይ መግለጫ በየበጀት ዓመቱ እስከ ግንቦት 30 ለኢንዱስትሪ ሚ/ር ሊያቀርብ ይገባል፡፡
	29. ኤጀንሲው የፈንዱን ሂሳብ አጠቃቀም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

ከ2-3 የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሂሳባቸውን ያዘገዩ የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ዝርዝር

ተ.ቁ	የድርጅቱ ስም	ያልተከፈለ ብር መጠን
1	አሰላ ብቅል ፋብሪካ	162,040,074
2	አዋሽ ወይን ጠጅ ፋብሪካ	81,399
3	ብሔራዊ አልኮልና አረቂ ፋብሪካ	24,391,613
4	አዳሚ ቱሉ ፀረ ተባይ ማዘጋጃ አ.ማህበር	17,688,158
5	የኮንስትራክሽ ዲዛይን አ.ማህበር	1,696,864
6	የሕንፃ አቅራቢዎች ድርጅት	853,003
7	የኢትዮጵያ እምነ በረድ ማምረቻ ድርጅት	16,314,438
8	ትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ዲዛይን	477,813
9	የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ስራ ድርጅት	33,865,828
10	የግዮን ሆቴሎች አስተዳደር	2,499,999
11	የፍል ውሃ አገልግሎት	6,812,309
12	የኢትዮጵያ ማዕድን ልማት አ.ማህበር	90,315,831
13	የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት አግልግሎት	1,457,931
14	የአርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት	22,237,018
15	ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት	32,887,671
16	ቦሌ ሚተሚያ ድርጅት	7,368,257
17	ንግድ ማተሚያ ድርጅት	7,776,246
18	የእርሻ መሳሪያዎች ቴክኒክ አገልግሎት አ.ማህበር	1,411,874
19	የተፈጥሮ ሙጫ ማምረቻ ድርጅት	25,236,068
20	የላይኛው አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት	1,565,264
21	ባሌ እርሻ ልማት ድርጅት	5,470,892
22	የኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ድርጅት	5,069,046
23	አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት	8,602,592

24	የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት	64,244,443
25	በከልቻ ትራንስፖርት አ.ማህበር	8,584,161
26	ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ	176,164,379
27	ኮሜት ትራንስፖርት አ.ማህበር	55,283,165
28	አበቦ እርሻ ልማት ድርጅት	6,556,335
ድምር		786,952,679.